ዘ ኢንሹራንስ
Z Insurance

# የዘመን ኢንሹራንስ አ/ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ (ማሻሻያ 1)

ታህሳስ 2014

CamScanner

# ማ ው ጫ


1. መግቢያ ________ 2
2. አጭር ርዕስ ________ 3
3. ትርጓሜ ________ 3
4. ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም ________ 3
5. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና ስብጥር ________ 4
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት ________ 5
7. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ________ 5
8. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ደንብ እና የአፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት ________ 5
9. እጩ የቦርድ አባላትን ጥቆማ የመቀበል እና የምልመላ ሂደት ________ 6
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት ________ 8
11. የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ________ 9
12. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ ________ 10
13. ዝርዝር የአጻጸም መመሪያ ስለማዘጋጀት ________ 10
14. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት ________ 11
15. የተሻሻለዉን መመሪያ በጥብቅ ስለመፈጸም ________ 11
16. መመሪያውን ስለማሻሻል ________ 11
17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ________ 11

## 1. መግቢያ

የዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመምረጥ ሥልጣን ለባለአክሲዮኖች የተሰጠ በመሆኑ፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ግልጽፅነት የሰፈነበት ማድረግ የመልካም አስተዳደር ዋና መርኾች ላይ ትኩረት ለመስጠት እና ለመተግበር የሚረዳ አንድ መሳሪያ በመሆኑ፣

በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚያገለግሉ ለቦታው የሚመጥኑ እና ተገቢ የሆኑ ዕጩዎችን የሚመለምል እና ለምርጫ የሚያቀርብ "የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ" ማቋቋም ሂደቱ ላይ ግልጽነት ለማምጣት እና በኢንሹራንስ በኩባንያው ውስጥ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ጠቃሚ በመሆኑ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይህ ኮሚቴ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ዘንድ እንዲቋቋም በመደንገጉ፣

ይህ "የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ" ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመለምላቸው እና ለምርጫ የሚያቀርባቸው እጩዎች በታው የሚጠይቀውን ታማኝነት፣ የአመራር ክህሎት እና ብቃት ያላቸው እንዲሁም ኢንሹራንስ ኩባንያው ስራ አስፈጻሚዎች የኩባንያውን ጥቅም ያስከብሩ ዘንድ አቅጣጫ የማስያዝ እና የመቆጣጠር አቅም ያላቸው እንዲሆኑ አደራ የተጣለበት በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣው የመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁ.SIB/48/2019 እንደተሻሻለ እና ሞዴል የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የመረጣ ሥነ-ሥርዓት ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ የሚቋቋምበትን እና ይህ ኮሚቴ ከተቋቋመ በኋላ የቦርድ አባላትን የምልመላ አካሄድ ለምርጫ የሚቀርብበትን ሁኔታ የሚወስን እና የሂደቱን ግልጽነት፣ ታማኝነት እና ፍትሐዊነት እንዲሁም የሚመረጡት አባላት ለቦታው የሚመጥኑ እና ተገቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መመሪያ ስለሚያስፈልግ፤ ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁ.SIB/48/2019 አንቀጽ 6.1.7 ላይ በተደነገገው መሰረት በዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ ሊወጣ ችሏል፡፡



CamScanner

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የዘመን ኢንሹራንስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሰራር መመሪያ (2021)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለዬ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

3.1. "**ኢንሹራንስ**" ማለት ዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ ነው።

3.2. "**ቦርድ**" ማለት ዘመን ኢንሹራንስ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው

3.3. "**ዋና የሥራ አስፈጻሚ**" ማለት የዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው

3.4. "**ዳይሬክተር**" ማለት የኢንሹራንስ ኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው።

3.5. "**ሠራተኛ**" ማለት የኢንሹራንስ ኩባንያው የዕለት ተዕለት ስራዎችን እንዲያካሄድ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው።

3.6. "**ጠቅላላ ጉባኤ**" ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ነው።

3.7. "**ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን**" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኩባንያው ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል 2% (ሁለት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው።

3.8. "**ኩባንያ**" ማለት ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ነው።

3.9. "**ተጽኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን**" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢንሹራንስ ኩባንያው ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ 2% (ሁለት በመቶ) በታች የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው።

3.10. "**ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው**" ማለት በኢንሹራንስ ኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ የሚቋቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ነው።

3.11. "**ብሔራዊ ባንክ**" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው።

4. **ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም**

4.1. ጠቅላላ ጉባኤው በሥራ ላይ ያለው ቦርድ የሥራ ጊዜውን ከማጠናቀቁ ከአንድ ዓመት በፊት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል። ኮሚቴው የሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከሚደረግበት ስድስት ወር በፊት ስራውን መጀመር አለበት። የኮሚቴው የሥራ ጊዜ የሚጠናቀቀው አዲስ የተመረጠው ቦርድ ሹመት በብሔራዊ ባንክ ሲጸድቅ ነው።

4.2. ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ 5 (አምስት) አባላት ይኖሩታል።

4.3. ይህን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና የምርጫ አሰራር መመሪያ ማጽደቅ የጠቅላላ ጉባኤው ሀላፊነት ነው፡፡

4.4. ጠቅላላ ጉባኤው 10 (አስር) እጩ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይጠቁማል፡፡ በአገኙት ድምጽ መሠረት አምስቱ ከተመረጡ በኋላ ሌሎች በድምጽ ቅደም ተከተል መሠረት ተጠባባቂ ሆነው ይያዛሉ፡፡

4.5. ጠቅላላ ጉባኤው ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በሚስጥር ድምጽ መስጫ ሥርዓት እንዲመረጡ ያደርጋል፡፡

4.6. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት የምርጫ ውጤት ምርጫው በተካሄደበት ዕለት ይፋ ይደረጋል፡፡

## 5. <u>የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና ስብጥር</u>

5.1. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት፤

(ሀ) ባለአክሲዮን መሆን አለባቸው፣

(ለ) የኮሚቴው አባል ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፣

(ሐ) ኢንሹራንስ ኩባንያው ሠራተኛ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆን የለባቸውም፣

(መ) ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ወይም ተመጣጣኙን ማጠናቀቅ አለባቸው እና

(ሠ) የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ተብሎ በወጡ የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር በማታለል ወይም እምነት በማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ያልሆነ፣

(ረ) ሌሎች በብሔራዊ ባንክና የአገሪቱ ንግድ ሕግ ላይ የተጠቀሱት ሕጎችን፣ ደንቦችን/መመሪያዎችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

5.2. ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ከአባላቱ መካከል የራሱን ሊቀ-መንበር/ሰብሳቢ እና ፀሐፊ መምረጥ አለበት፣

5.3. ጠቅላላ ጉባኤው የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር የትኛውንም ቢሆን፣ ከአባላቱ ውስጥ ቢያንስ 2ቱ (ሁለቱ) ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

5.4. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በዚህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሰራር መመሪያ ላይ ኢንሹራንስ ኩባንያው የሚያዘጋጀውን ስልጠና መውሰድ አለባቸው፡፡

## 6. <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት</u>

**የዳይሬክተሮች ቦርድ፣**

6.1. የዳሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲመረጡ የማስደረግ፣

6.2. ለጠቅላላ ጉባኤው በሚቀርበው አጀንዳ ውስጥ የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ተካቶ እንዲቀርብ የማድረግ፣

6.3. ለአስመራጭ ኮሚቴው የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኝ የማድረግ፣ ኃላፊነት አለበት፡

## 7. <u>የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

7.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምልመላ እና ምርጫ ሙሉ ሂደትን የማስፈጸም፣

7.2. በመጀመሪያ ቀን ስብሰባው የራሱን ሊቀ-መንበር እና ፀሐፊ የመምረጥ፣

7.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሰራር መመሪያ ላይ የሚሰጥን ስልጠና የመውሰድ፣

7.4. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የእጩዎችን ጥቆማ የመቀበል፣

7.5. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የእጩ ተወዳዳሪዎችን ጥቆማ ማቅረብም ሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ሂደት ግልጽነት የተሞላበት፣ በአግባቡ የተካሄደና እምነት የሚጣልበት መሆኑን እና አግባብነት ባለው ህግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና በዚህ መመሪያ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።

## 8. <u>የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ደንብ እና የአፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት</u>

8.1. ኮሚቴዉ ስብሰባ የሚያደርግበትን ቀን፣ ሰዓቱንና ቦታውን እንዲሁም የስብሰባዉን አካሄድ የሚገልጽ የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል።

8.2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮሚቴው ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

8.3. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሟላል።

8.4. የኮሚቴው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፣ ሆኖም የኮሚቴው አባላት በእኩል ሲካፈሉ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

8.5. የኮሚቴው ሰብሳቢ የኮሚቴው መሪ ሆኖ ስብሰባውን የመምራት፣ ጊዜን የመወሰን እና ስብሰባዎችን የመምራት፣ አጀንዳ የማዘጋጀትና የደብዳቤ ልውውጦችን የማስተናገድ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ፀሐፊው ደግሞ የኮሚቴውን ስብሰባ ሂደቶች እና ውሳኔዎች በቃለ-ጉባኤ ይይዛል።

8.6. ቃለ-ጉባኤዎች ተከታታይ ቁጥር ይዘው በተሰብሳቢዎች ሁሉ መፈረም አለባቸው።

8.7. ከአስመራጭ ኮሚቴው ውስጥ 50% በታች የሚያንሱት አባላት የኮሚቴውን ሥራ ከአቋረጡ፣ ቀሪዎቹ አባላት ከተጠባባቂዎች ውስጥ ኮሚቴው ሲቋቋም በአገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሠረት እንዲተኩ ይደረጋሉ።

8.8. በስራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከግማሽ (50%) በታች በሆነ ጊዜ ግን የኮሚቴው አባላት በተጓደሉ የኮሚቴ አባላት ምትክ በተጠባባቂነት ከተያዙት ውስጥ ለመተካት ስለማይችሉ ጉዳዩን ስራ ላይ ላለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት በማድረግ ስራውን መተው አለባቸው።

8.9. በተራ ቁጥር 8.8 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ስራውን ከተወ በስራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ይህንኑ ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ማድረግና ጉዳዩን አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች በተደነገገው መሠረት መፈጸም ይኖርበታል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በተደነገገው መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲመረጡ ያደርጋል።

8.10. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ኃላፊነቱን ግልጽነት በተሞላበት፣ በአግባቡና እምነት በሚጣልበት መልኩ ሳያከናውን ከቀረ እና በብሔራዊ ባንክ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች እና በኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ የተመለከቱትን ሳይከተል ቀርቶ የምርጫው ውጤት ከተሰረዘ ለኮሚቴው ከሚከፈል ክፍያ በማይበልጥ መቀጮ የሚቀጣ ይሆናል።

## 9. <u>እጩ የቦርድ አባላትን ጥቆማ የመቀበል እና የምልመላ ሂደት</u>

9.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ባለአክሲዮኖች ለዳይሬክተሮች ቦርድ የእጩዎች ጥቆማ መጀመሩን ሰፊ ስርጭት ባለው የህትመትና ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ብዙሀን ጥሪ ማስተላለፍ አለበት፤ ባለአክሲዮኖች የእጩዎች ጥቆማ እንዲያደርጉ መጋበዝ አለበት።

9.2. ኮሚቴው የሚጠቆሙትን እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ መመዘኛና የጥቆማ ማቅረቢያ ፎርሙን በማስታወቂያው አካቶ መግለጽ አለበት፣

9.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የእጩዎች ጥቆማ ግዜ የሚያበቃበትን ቀን መግለጽ አለበት። ይሁን እንጂ ለጥቆማ የሚሰጠው ጊዜ ከሰስት ወራት ያነሰ መሆን የለበትም።

9.4. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ለቦርድ አባልነት እጩ ሆነው አይቀርቡም።

9.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስፈልግ ጊዜያዊ ቢሮና ሰራተኞችን በመያዝ ስራውን ያከናውናል። ኮሚቴው መዝገብ በማዘጋጀት እጩ ተጠቋሚዎችን በመዝገብ ይመዘግባል።

9.6. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት እጩዎችን ለመጠቆም የሚያስችሉ አመቺና በቂ የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም እጩዎችን እንዲጠቁሙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ለሁሉም ባለአክሲዮኖች እድል መስጠት አለበት።

9.7. የእጩዎች ምልመላ የሚደረገው በጥቆማዉ ወቅት እጩዎች ባገኙት የጥቆማ ድምጽ መሠረት ሲሆን አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

9.8. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤-

ሀ. ከእጩ ተጠቋሚዎች መካከል 1/3ኛው እጩ ተጠቋሚዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የተጠቆሙና የተመረጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ተብለው የሚወሰዱት ባለአክሲዮኖች ከኩባንያው የተፈገመ ካፒታል 30 በመቶ በታች ድርሻ መያዝ ይኖርባቸዋል፤

ለ. ከእጩ ተጠቋሚዎች መካከል 1/4ኛው እጩ ተጠቋሚዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የተጠቆሙ እና የተመረጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ተብለው የሚወሰዱት ባለአክሲዮኖች ከኩባንያው የተፈረመ ካፒታል 30 በመቶ በታች ድርሻ መያዝ ይኖርባቸዋል እና፣

ሐ. የተቀሩት 2/3ኛው ወይም ¾ኛው ተጠቋሚ እጩዎች ደግሞ መጠቆምና መመረጥ ያለባቸው በሁሉም ባለአክሲዮኖች ነው።

9.9. ከላይ በቁጥር 9.8 የተጠቀሰውን ስብጥር ለመጠበቅ 2/3ኛ ወይም 3/4ኛ እጩ ተጠቋሚዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙ እጩዎች የሚወሰዱ ሲሆን ቀሪዎቹ 1/3ኛ ወይም 1/4ኛ ደግሞ ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ብቻ ይወሰዳሉ።

9.10. በተራ ቁጥር 9.8 የተጠቀሰው ስብጥር በባለ አክሲዮኖች የእጩዎች ጥቆማ ወቅት ካልተጠበቀ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ይህ ስብጥር እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ተገቢውን ስብጥር ለመጠበቅ ኮሚቴው በቅድሚያ 1/3ኛውን (ወይም 1/4ኛውን) እጩ ተጠቋሚዎችን ከለየ በኋላ 2/3ኛውን (ወይም 3/4ኛውን) ደግሞ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ይወስዳል። ይህንኑ ስብጥር ለማረጋገጥ ኮሚቴው በመጀመሪያ 1/3ኛውን (ወይም 1/4ኛውን) እጩ ተጠቋሚዎችችን ከለየ በኋላ ወደ 2/3ኛዉ (ወይም 3/4ኛዉ) እጩ ተጠቋሚዎች ያመራል።

9.11. በእጩነት የሚጠቆሙት የእጩ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ተወዳዳሪዎች ቁጥር በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ከሚሾሙት ቁጥር ቢያንስ እጥፍ መሆን አለበት በተጨማሪ ኮሚቴው 9 (ዘጠኝ) እጩ ተወዳዳሪዎችን በተጠባባቂነት እንዲያዙ ያደርጋል።

9.12. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ተጠቋሚዎችን ለመለየት የሚጠቀመዉ ተጠቋሚዎች ባገኙት የድምጽ መጠን ሲሆን ድምጹም የተፈረመ የአክሲዎን መጠን ላ ይ የተመሰረተ ይሆናል። እኩል ድምጽ ያገኙ እጩ ተጠቋሚዎች ቢያጋጥሙ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ልምድና ሌሎችም አግባብነት አላቸዉ ተብሎ የታመነባቸዉን ምክንያቶች ኮሚቴዉ በመጠቀም እጩዉን ለይቶ ያቀርባል።

9.13. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የለያቸዉን እጩዎች ዝርዝር ካገኙት የጥቆማ ድምጽ ጭምር በሚከተሉት ሁኔታዎች መግለጽ አለበት፤

ሀ. በኩባንያው ዋና መ/ቤት እና ቅርንጫፎች ሁሉም ሰዉ በሚያየዉ ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፤

ለ. ሰፊ ሽፋን ባላቸው ጋዜጦች ላይ እንዲወጣ ያደርጋል፤ እንዲሁም

ሐ. በኩባንያው ድረ-ገፅ ፤ቢያንስ ምርጫ ለማካሄድ ጠቅላላ ጉባዔ ከመካሄዱ አንድ ወር በፊት ያወጣል።

9.14. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ የመለመላቸውን እጩ-ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባኤ ሲያቀርብ እያንዳንዱ እጩን በተመለከተ ቢያንስ የሚከተሉትን የተጠቃለሉ መረጃዎች ጨምሮ ማቅረብ አለበት፡

ሀ. ስምና እድሜ፣

ለ. ያገኘውን የድምጽ ብዛት፣

ሐ. የትምህርት ደረጃ፣

መ. የሥራ ልምድ፣

ሠ. በአሁኑ ሰዓት በሌላ ተቋም በቦርድ ወይም በሌላ ኃላፊነት ያለው የአባልነት ሁኔታ

9.15. የእጩ ተጠቋሚዎችን ዝርዝር በተመለከተ የቀረበዉ የዉሳኔ ሀሳብ ስለዳይሬክተሮች ቦርድ ስብጥር በኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች እና በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን ኮሚቴዉ ማረጋገጥ አለበት።

9.16. የቀረቡ እጩ ተጠቋሚዎች ብዛት በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ከጠቀመዉ በታች ሲሆን ወይም እጩ ተጠቋሚዎች በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን ካላሟሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴዉ በራሱ የተቻለዉን ጥረት ሁሉ በማድረግ የእጩዎች ቁጥር በመመሪያዉ ከተመለከተዉ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ይኖርበታል። ነገር ግን ኮሚቴዉ ተገቢዉን ጥረት አድርጎ የሚፈለገዉን የእጩዎች መጠን ለማግኘት ካልቻለ ይህንኑ ሁኔታ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ሪፖርት በማድረግ በጠቅላላ ጉባኤዉ ምርጫ ይደረጋል።

## 10. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት

10.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴዉ ከጠቅላላ ጉባኤው(ሰብሳቢ፣ ድምጽ ቆጣሪዎች እና የማህበሩ ጸሀፊ) ጋር በመተባበር የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደትን የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት።

10.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ እጩ ተጠቋሚዎችን ከተገቢ መግለጫ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤዉ ያቀርባል።

10.3. ኮሚቴው ተወዳዳሪዎች ራሳቸውን ለጉባኤው እንዲያስተዋውቁ፣ የቦርድ አባል ሆነው ለመስራት ፈቃደኝነታቸዉንም እንዲያረጋግጡ ያደርጋል።

10.4. ኮሚቴው ከሚመለከተው የኩባንያው የሥራ ክፍል ጋር በመተባበር ባለአክሲዮኖች የሚመርጡበትን የሚስጥር ድምጽ መስጫ ካርድና ሳጥኖች ያዘጋጃል።

10.5. የሚስጥር ድምፅ መስጫው ካርድ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ. የባለአክሲዮኑን ስም፣

ለ. ባለአክሲዮኑ ያለውን የተፈረመ የአክስዮን መጠን/ብዛት፣

ሐ. የስብሰባ ተካፋይነት ልዩ መታወቂያ ቁጥር

መ. የኢንሹራንስ ኩባንያውን ስምና አርማ፣

ሠ. የኢንሹራንስ ኩባንያውን ማኅተም፣

ረ. ባለአክሲዮኑ የሚመርጣቸውን እጩዎች የሚጽፍበት ባዶ ቦታ፣

10.6. ባለአክሲዮኖች በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት ፊርማ በሚፈርሙበት ጊዜ የድምጽ መስጫ ካርዶች ለባለአክሲዮኖች ይሰጣል። በተጨማሪም የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የምርጫ ሂደቱን በቅርበት መከታተል ይኖርበታል።

10.7. ከእጩ ተጠቋሚዎች መካከል የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ ፈቃደኛ የማይሆን ቢኖር ወይም በሌላ ምክንያት ጥቆማዉ ተቀባይነት ካላገኘ በተጠባባቂነት ከተያዙት እጩ ተጠቋሚዎች በቅደም ተከተል በመተካትና ተመሳሳይ ስነስርዓትን በመከተል ምርጫዉ እንዲካሄድ ይደረጋል።

## 11. የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት

11.1. ኮሚቴዉ የመራጮችን ድምፅ የሚቀበለዉ ለምርጫው ሲባል ቀደም ብሎ በተዘጋጀ የምርጫ ሳጥን ዉስጥ ድምጽ የሠጡበትን ካርድ እንዲከቱ በማድረግ ነዉ።

11.2. ባለአክስዮኖች ምርጫዉን በሚያደርጉበት ወቅት በድምጽ መስጫ ካርዱ ላይ በአንቀፅ 10.5 ላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች በሙሉ መገኘታቸዉን በማረጋገጥ የመረጡትን እጩ ተወዳዳሪ ስም በመሙላት እና በመፈረም ለምርጫ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይከታሉ።

11.3. በግንባር ወይም በተወካይ ድምጽ መስጠት የሚቻለዉ በኩባንያዉ መመስረቻ ጽሁፍ በተገለጸዉ መሰረት ነዉ። ሆኖም ባለአክሲዩኑ የእራሱንና የሚወክለዉን ሌላ ባለአክሲዎን ጨምሮ ከኩባንያዉ የተፈረመ ካፒታል ከ10% የበለጠ ወክሎ ሊቀርብ አይችልም።

11.4. የምርጫው ሂደት እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ኮሚቴው ከጉባኤው (ሰብሳቢ፣ድምጽ ቆጣሪዎችና የማህበሩ ጸሃፊ) ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመሆን የድምጽ ቆጠራውን ያከናውናል።

11.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ለእያንዳንዱ እጩ ተመራጭ የተሰጠዉን ድምጽ፣ ዉድቅ የተደረጉ የድምጽ መስጫ ካርዶችን መመዝገብና ይህም ሲያጋጥም በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ ምክንያቱ ተጽፎ በምልመላና አስመራጭ ኮሚቴዉ መፈረም አለበት።

11.6. የድምፅ መስጫ ካርዱ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ዉድቅ ሊሆን ይችላል፤

ሀ. የባለአክሲዩኑን ስም ካልተጻፈበት፣

ለ. የባለአክሲዮኑን የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት ያልጠቀሰ ከሆነ፣

ሐ. የኩባንያው ስምና አርማ ካልያዘ፣
መ. የእጩ ተወዳዳሪው ስም ካልተጻፈበት፣
ሰ. ያልተፈረመ ከሆነ፣
ረ. ስርዝ ድልዝ ከሆነ፣
ሸ. የባለአክሲዮኑን የስብሰባ ተካፋይነት ልዩ መታወቂያ ቁጥር ካልተጠቀሰ፣

11.7. የድምጽ ቆጠራው ሂደት ከተጠናቀቀ በኃላ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የድምጽ አሰጣጡንና የቆጠራውን ሂደት እንዲሁም የዉጤቶቹን ተቀባይነት በተያዘዉ ቃለ- ጉባኤ እና ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀዉ ቅጽ ላይ በመፈረም ማረጋገጥ አለበት።

11.8. ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠዉና የተቆጠረው ድምፅ ታሽጎ ለብቻው መቀመጥ አለበት።

11.9. የቆጠራው ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤው በዕለቱ መገለጽ አለበት፣ ይህን ማድረግ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ በቀጣዩ የሥራ ቀን በኩባንያው ዋና መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና ዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ ድረ-ገጽ ላይ መስፈር አለበት።

## 12. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ

12.1. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆነው ስራ ላይ ካሉት የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት፣
ሀ. የስራ ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት በጠቅላላ ጉባኤ ወይም በብሔራዊ ባንክ ከስራቸው እንዲነሱ ከተደረገ፣
ለ. በገዛ ፈቃዳቸው ከቦርድ አባልነት ከለቀቁ፣
ሐ. በተለያዩ ምክንያቶች በቦርድ አባልነት መቀጠል ካልቻሉ ወይም
መ. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴዉ የቀረቡ ዕጩ ተጠቋሚዎች ከ50 በመቶ በላይ በሆነ ድምጽ በጠቅላላ ጉባኤው ተቀባይነት ካጡ።

12.2. በአንቀጽ 12.1. ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ስለቦርድ አባላት ምርጫ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ውስጥ የሚገኙ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

12.3. በስራ ላይ ያሉት የቦርድ አባላት ከግማሽ በታች ከሆኑ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ በማድረግ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ መደረግ አለበት።

## 13. ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ስለማዘጋጀት

የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚረዳ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አለበት።

## 14. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ተግባራዊ ሲደረግ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ሕጎችና የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ።



CamScanner

## 15. የተሻሻለው መመሪያ በጥብቅ ስለመፈጸም

የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ የጸደቀውን የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ (ማሻሻያ 1) በጥብቅ እንዲፈጸም ያደርጋል፤ ራሱም በጥብቅ ይፈጽማል።

## 16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ማሻሻያውን የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን እስካልተቃረነ ድረስ ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ (ማሻሻያ 1) በጠቅላላ ጉባኤው ሊሻሻል ይችላል።

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ዉሳኔዉ የተላለፈበት ቃለ ጉባኤ አግባብነት ባላቸዉ የመንግስት አካላት ተረጋግጦ ሲጸድቅ ነዉ።